**፲፩· የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እድሳት**

፩· የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ የምስክር ወረቀቱ የሚያገለግልበት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የእድሳት ማመልከቻውን ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት።

፪· ኤጀንሲው የአመልካቹን የሥራ ክንውንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሁኔታዎች ከገመገመ በኋላ ማመልከቻው በደረሰው በ፲፭ ቀን ውስጥ የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ያድሳል።

**፲፪· የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለመሰረዝ እና ስለማገድ**

፩· ኤጀንሲው በሚከተሉት ምክንያቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ሊሰርዝ ይችላል፤

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማታለል ወይም የሀሰት መረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ መሆኑ ሲታወቅ፣

ለ) ኤጀንሲውን ሳያስፈቅድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ለሌላ ሰው ካስተላለፈ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ በተደነገገው መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ካላሳደሰ፤

መ) የዕጽዋት ዘር የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ያላሟላ ዘር ሲሸጥ ከተገኘ፤

ሠ) የንግድ ፈቃዱ የተሠረዘበት ከሆነ።

፪· የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠባቸው ዝርዝር ሁኔታዎች ውጭ የምስክር ወረቀቱ ባለቤት ሠርቶ ቢገኝ ኤጀንሲው የምስክር ወረቀቱን ሊያግደው ወይም ሊሰርዘው ይችላል።

፫· ኤጀንሲው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን እንደ ሰረዘ የንግድ ፈቃዱም እንዲሰረዝ ለፈቃድ ሰጭው አካል በጽሑፍ ያሳውቃል።

**፲፫· መረጃ ስለመያዝና ስለማቅረብ**

ማናቸውም የተደነገገ ዘር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት የሆነ አምራች፣ አዘጋጅ፣ አስመጪ፣ ላኪ፤ አከፋፋይ፣ ቸርቻሪ፣

፩· የእያንዳንዱን ማሳ፣ ያመረተውን ዘር፣ ያዘጋጀውን ዘር፤ ያስመጣውን ዘር፣ የላከውን ዘር፤ ያከፋፈለውንና የቸረቸረውን ዘር፣ በዝርዝር መዝግቦ ይይዛል፤

፪· መረጃዎችንና ትንተና የተካሔደባቸውን የዕፅዋት ዘር ናሙናዎች ይይዛል፣ ትንተና የተካሔደባቸውን የዕፅዋት ዘር ናሙናዎችን በተመለከተ ለአንድ ዓመት መያዝ አለበት፣ ናሙናዎችን እንደአስፈላጊነቱ ከዚህም በላይ መያዝ ይችላል።

፫· ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የያዘውን መረጃ ለኤጀንሲው ይልካል፣ እንዲሁም የኤጀንሲው ኢንስፔክተር መረጃውን ለቁጥጥር በጠየቀ ጊዜ ያቀርባል፣

## ክፍል ሦስት
## ስለ ዕጽዋት ዘር ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ ግብይትና ጥራት ቁጥጥር

**፲፬· ስለ አመራረት፣ አዘገጃጀትና ግብይት**

ማንኛውም በሀገር ውስጥ የሚመረት፣ የሚዘጋጅ፣ ከውጭ የሚመጣና ወደ ውጭ የሚላክ ፣ የሚሸጥና የሚሠራጭ የዕፅዋት ዘር ዝርያው በኤጀንሲው የተመዘገበና ዘሩ የኢትዮጵያን የዘር ደረጃዎች እና መስፈርቶች ያሟላ መሆን አለበት።

11. *Renewal of Competence Assurance Certificate*

1) Every holder of a certificate of competence assurance, desiring to renew the certificate, shall make an application to the Agency in accordance with the form designed for this purpose, within one month before the date of expiry of the said certificate.
2) On receipt of an application for renewal the Agency shall, evaluate the performance of the applicant and other relevant circumstances, and by charging service fee renew the certificate of competence assurance within 15 days period.

12. *Cancellation and Suspension of Certificate of Competence Assurance*

1) The Agency may cancel a certificate of competence assurance on any of the following grounds;
   (a) where the certificate has been obtained by fraud, false documents or misrepresentation as to material particulars;
   (b) where the certificate has been transferred to any other person without prior permission of the Agency;
   (c) where the certificate has not been renewed pursuant to the provisions of Article 11 of this Proclamation;
   (d) where the holder of the certificate of competence assurance has been found selling sub-standard seed;
   (e) where the license for seed business has been cancelled;
2) The Agency may suspend or cancel the certificate if the owner of the certificate has been found using it for other purposes than the terms and conditions it has been issued for.
3) The Agency after having cancelled the certificate of competence assurances shall notify, same in writing to the licensing Authority to cancel his/her seed business license;

13. *Keeping and making Available Records*

Any owner of Competence Assurance Certificate as producer, processor, importer, exporter, distributor and retailer shall:

1) record and keep particulars of each field, seed produced, seed processed, seed imported and exported, and seed distributed and retailed;
2) keep records and seed samples on which analysis have been made keeping. The period for keeping seed samples on which analysis have been made should be one year; keeping samples may also be for more years, as the case may require.
3) transmit to the Agency such records kept as provided under Sub-Articles (1) and (2) hereof and submit same for inspection where requested by the Inspector.

## PART THREE
## Production Processing, Marketing and Quality Control

14. *Seed Production, Processing and Marketing*

Any seed produced and processed locally, or imported or to be exported, or to be sold and distributed in the country shall be a variety registred by the Agency and shall conform to the requirements and seed standards of Ethiopia.

፲፭· ስለጥራት ቁጥጥር

፩· ማንኛውም የተደነገገ ዘር አግባብ ያለውን የኢትዮጵያን የዘር ደረጃና መስፈርት ማሟላት ይኖርበታል። የዚህም ተግባራዊነት በኤጀንሲው በኩል ይረጋገጣል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ኢንስፔክተሩ በማናቸውም ማምረቻ፣ ማዘጋጃ፣ ማከማቻ ፣ ማከፋፈያና መቸርቸሪያ ሥፍራዎች ሁሉ በመገኘት ማናቸውም የተደነገገ ዘር ከተወሰነው የኢትዮጵያ የዘር ደረጃ ጋር መጣጣሙን ይቆጣጠራል፤ እንደአስፈላጊነቱም ማሻሻያዎች፣ (ማስተካከያዎች) ፣ እንዲደረጉ ባለቤቱን ይመክራል፤ ባለቤቱም ምክሩን ተቀብሎ አስፈላጊውን ማሻሻያ ፣ (ማስተካከያ)፣ ማድረግ ይኖርበታል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ማናቸውም የተደነገገ ዘር ከተሻሻለ ወይም ከተስተካከለ በኋላ ባለቤቱ የዘሩን ናሙና ለተጨማሪ ምርመራ ወደ ምርመራው ማዕከል እንዲልክ ኢንስፔክተሩን ሊጠይቀው ይችላል። የዘር መርማሪውም ዘሩ ልዩ ዓይነት ምርመራ የሚፈልግ ካልሆነ በስተቀር የተደነገገው ዘር ከተወሰነው የኢትዮጵያ የዘር ደረጃ ጋር መጣጣሙን ለማረጋገጥ የዘር ናሙናውን ለድጋሚ ምርመራ በመላክ ምርመራ ማዕከሉ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በ፲፭ ቀን ጊዜ ውስጥ ውጤቱን ለዘሩ ባለቤት መግለጽ ይኖርበታል። የዘሩ ባለቤትም እስከዚያው ጊዜ ድረስ የተደነገገውን ዘር ለዘር አገልግሎት መሸጥ አይችልም።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ለሚደረገው ተደጋጋሚ የዘር ምርመራ ባለቤቱ ለእያንዳንዱ ለሚደረገው ምርመራ የተወሰነውን ክፍያ ይከፍላል።

፭· ኤጀንሲው በማንኛውም ጊዜ በመጋዘንና በሽያጭ መደርደሪያ ላይ ለሽያጭ የተዘጋጁ ዘሮችን ናሙና በመውሰድ የዘር ደረጃው በዘር ጥራት መግለጫው መሠረት መሆኑን ቁጥጥር ያደርጋል፤ ውጤቱም መግለጫው ላይ ከተመለከተው አንሶ ሲገኝ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል።

፲፮· መለያ ምልክት ስለማድረግ

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በአንቀጽ ፲፭ መሠረት የተመረመረ ማናቸውም የተደነገገ ዘርን የሚሸጥና በአንቀጽ ፲፯ ላይ የተገለጹትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ማንኛውም የተመዘገበ የዘር ሻጭ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባሮች የመፈጸም ግዴታ አለበት፤

ሀ) የአምራቹ ስምና አርማ

ለ) እንደሁኔታው "የተመሰከረለት ዘር የሀገር ውስጥ" ወይም "የተመሰከረለት ዘር የውጭ" የሚል ቃል፤

ሐ) የተደነገገው ዘር የተመረተበት ዓመተ ምህረት እና የተመረመረበት ቀን እና ዓመተ ምህረት፣

መ) የሰብል ዓይነትና የዝርያ ስም፣

ሠ) ሌሎች የዘሩን የጥራት ሁኔታ የሚገልጹ ዝርዝሮችን፤ በመመሪያው መሠረት መያዣው ላይ እንዲታተም ወይም በተወሰነ የዘር ደረጃ መግለጫ ላይ በማይለቅ ቀለም ተጽፈው ከውጭ እንዲለጠፉ እና ከውስጥም እንዲደረጉ ያደርጋል።

፲፯· የዘር ሽያጭን ስለመቆጣጠር

፩· ማንኛውም ሰው በብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላይ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሠረት የዘር ሻጭ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሌለው በስተቀር ማናቸውንም የተደነገገ ዘር ለመሸጥ አይችልም።

15. *Quality Control*

1) Any prescribed seed shall conform to the requirements of the appropriate Ethiopian Seed Standards and such conformity shall be ascertained by the Agency.

2) The inspector shall, pursuant to Sub-Article (1) of this Article, appear at production, processing, storage, wholesale and retail sites of a prescribed seed and inspect conformity to the designated Ethiopian Standards. He shall also advise the owner of a seed, as may be necessary, to take corrective measures towards improving his seed's standards. The owner of the seed must, pursuant to the advice, make the necessary improvement.

3) Where any prescribed seed has been improved pursuant to Sub-Article (2) of this Article, the owner may request the seed-inspector to send his seed sample to a seed-testing center for further lest. The seed inspector shall notify the owner of the seed, within 15 days starting from the date of receipt of the sample by the seed testing center, the conformity of the prescribed seed to the Ethiopian Seed Standard provided the seed does not require special test. Until such time, the owner cannot offer the prescribed seed for sale.

4) Where repeated testing of such a seed as prescribed in Sub-Article (3) of this Article is made, the owner shall pay such fees as may be prescribed for each test.

5) The Agency may, at any time, take seed samples from stores, wholesale and retail shops and conduct laboratory tests to check whether the sample conforms to the particulars indicated on labels and take legal measures whenever lower test results are observed.

16. *Labeling*

Without prejudice to the provisions of this Proclamation, any registered seed seller who sells any prescribed seed which has been tested in accordance with Article 15 and found complying with the provisions of Article 17 has the obligation to cause the printing or stamping with an indelible ink upon such container or upon a specified lable attached thereto and enclosed therein the following particulars in accordance with the directives:

(a) the name of the producer and its emblem;
(b) the words "Certified Seed Local" or "Certified Seed Imported" as the case may be;
(c) year of prduction and the date on and year within which the prescribed seed was tested;
(d) type of crop and name of the variety; and
(e) other particulars specifying the seed quality.

17. *Control of Sale of Seed*

1. No person shall sell any prescribed seed unless he has a seed seller's competence assurance certificate issued in accordance with the terms and conditions specified in the competence assurance certificate.

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት፡

ሀ) አስመርማሪው ከራሱ የምርመራ ማዕከል ውጭ ለሚያረገው የተደነገገ ዘር ናሙና ምርመራ የተወሰነውን ክፍያ ምርመራውን ለአከናወነው የምርመራ ማዕከል የመክፈል ግዴታ አለበት።

ለ) የተወሰደው ናሙና በዘር ምርመራ ማዕከል እንደ ደረሰ የተመደበው የዘር ተንታኝ የተወሰነውን መመሪያ በመከተል በናሙናው ላይ ምርመራ አካሂዶ ምርመራው እንዲካሄድለትና የምርመራው ውጤት እንዲደርሰው ለፈለገው ሰው የምርመራውን ውጤትና ለሪፖርቱ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች ዝርዝሮች በመግለጽ ይሰጣል።

## ፳፬· ስለዘር ኢንስፔክሽንና የዘር ኢንስፔክተር ተግባርና ኃላፊነት

፩· ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል ኤጀንሲው የዘር ኢንስፔክተር ይመድባል።

፪· ኤጀንሲው ለእያንዳንዱ የዘር ኢንስፔክተር የመቆጣጠር ሥልጣን እንዳለው የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፫· የዘር ኢንስፔክተሩ በኤጀንሲው በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ቁጥጥሩ የሚካሄድበት ማንኛውም ሰው በጠየቀ ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን የምስክር ወረቀት ማሳየት አለበት።

፬· የዘር ኢንስፔክተሩ፡

ሀ) ዘሩ የተደነገገ ዘር መሆኑን ለመወሰን እንዲቻል፡

ለ) የተደነገገው ዘር በዚህ አዋጅ መሠረት ከተወሰነው የጥራት ደረጃ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ ይችል ዘንድ ምርመራ ለማካሄድ፡ እና

ሐ) በኤጀንሲው በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አስፈላጊ ነው ብሎ ላመነባቸው ለሌሎች ምክንያቶች ሁሉ፡

የዘር ወይም የተክል ናሙናዎችን ሊወስድ ይችላል።

፭· የዘር ኢንስፔክተሩ አዋጁን ለማስፈጸም ሲባል በማናቸውም ተገቢ በሆነ ሰዓት ይህንን አዋጅ በመጣስ የተደነገገ ዘር ንግድ ይካሄድበታል ብሎ የሚያምንባቸውን ማናቸውንም ማሣዎች፡ መጋዘኖች፡ ዘር የጫኑ መኪናዎች፡ እና የዘር ማበጠሪያዎችን በመፈተሽ ሥራው ትክክል አለመሆኑን ሲያረጋግጥ እንቅስቃሴውን ማገድ ይችላል።

፮· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የዘር ኢንስፔክተሩ፡

ሀ) ስለእገዳው ሥራው ለታገደበት ሰው የጽሁፍ ማስረጃ ይሰጣል።

ለ) ለኤጀንሲው የዕገዳውን ዝርዝር ሁኔታ በመግለጽ ኤጀንሲው በአሥራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል።

## ፳፭· ዘር ከውጭ ስለማስገባትና ወደውጭ ስለመላክ

፩· የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የያዘና ዘር የማስገባትና የማስወጣት ፈቃድ ከኤጀንሲው ያገኘ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው የተደነገገ ዘርን ለሽያጭ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ወይም ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ለመላክ አይችልም።

፪· ማንኛውም የዘር አስመጪ ወይም ላኪ የተደነገገ ዘርን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ወይም ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ለመላክ የሚችለው፡

ሀ) ዘሩ የተገደበ ዘር ያልሆነ ሲሆን፡

ለ) ዘሩ የኢትዮጵያን የዘር ደረጃዎች እና መስፈርቶች ያሟላ ሲሆን፡

3) Pursuant to Sub Article (1) of this Article;

(a) A person who seeks the testing of a sample of prescribed seed outside his own testing center, shall pay the prescribed fee to the center performing the test.

(b) Upon receipt of any sample drawn at the seed testing center the official seed analyst shall analyze the sample in prescribed procedure and provide the person who sought the test with the report thereof, the findings therein and such other particulars as may appear necessary for or relevant to the report.

## 24. *Seed Inspection and Duties and Responsiblities of Inspectors*

1) The Agency shall appoint a Seed Inspector for the implementation of this Proclamation.

2) The Agency shall issue to each seed inspector a certificate which shows his authority to inspect.

3) A seed inspector shall produce his certificate of authority given to him pursuant to Sub–Article (2) of this Article, upon request of the person affected by the inspector in the course of exercising any of his powers given to him by the Agency.

4) A Seed Inspector may take samples of any seed or plant for any of the following purposes:

(a) to determine whether the seed is a prescribed seed;

(b) to test a seed in order to determine that the prescribed seed conforms to the quality standards prescribed under this Proclamation;

(c) for such other purposes as he may deem necessary in relation to the powers given to him by the Agency.

5) A seed Inspector may, for the implementation of this Proclamation, at any reasonable time any field, store, vehicle which carries seed and seed processing plant which he has reasonable cause to believe that it is being used in the business of prescribed seed in violation of this Proclamation and when he confirms that the Proclamation has been violated, may suspend the operation of such business.

6) The inspector shall, pursuant to powers given to him under sub–Article (5) of this Article:

(a) give a written evidence to the person whose business is suspended.

(b) report to the Agency the details of suspension to enable the Agency to take appropriate measures within 15 days;

## 25. *Import and Export of Seeds*

1) No person shall import into or export from Ethiopia for sale any prescribed seed unless he is a holder of competence assurance certificate and has obtained seed import or export permit from the Agency.

2) any seed importer or exporter shall import into Ethiopia or export from Ethiopia any prescribed seed where:

(a) such seed is not a restricted Seed;

(b) such seed conforms to the Ethiopian Seed Standards and requirements;

## ክፍል አራት
## የኤጀንሲው የሥራ ድርሻ

፳፱· **የአጽዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የማንኛቸውም ዕፅዋት አዲስ ዝርያ የሚገመገመው እና የሚጸድቀው አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ተውጣጥቶ በተቋቋመው ብሔራዊ የዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ነው።

፴· **የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት**

ኤጀንሲው ፡ በማቋቋሚያ አዋጁ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፡

፩· ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትንም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚመረቱትን ዝርያዎች ይወስናል፡

፪· ዓመታዊ የዝርያዎች ዝርዝር (ሬጅስተር) አዘጋጅቶ ያወጣል፡ ሬጅስተሩ ለተጠቃሚዎች መድረሱን ይከታተላል፡ ያረጋግጣል፡

፫· የዕፅዋት ዘር ማምረት፡ ማዘጋጀት፡ ማስመጣት፡ መላክ፡ በጅምላና በችርቻሮ መሸጥን በተመለከተ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡ ያድሳል፡ ያግዳል፡ ይሰርዛል፡

፬· የተደነገገ ዘር ምርመራ የሚከናወንባቸውን የዘር ምርመራ ማዕከላትን ያቋቁማል፡ ለተቋቋሙት ወይም ለሚቋቋሙት ማዕከላት ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡

፭· በአዋጁ መሠረት የዘር ምርመራ ያከናውናል፡ የዘር ተንታኞችንም ይመድባል፡

፮· ኤጀንሲው በማንኛውም ጊዜ የተመረተውን፡ የተበጠረውንና ለንግድ የተዘጋጀውን ዘር ናሙና ወስዶ ትንተና ማካሄድ ይችላል፡

፯· ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የኢንስፔክሽን ቡድን አቋቁሞ ኢንስፔክተሮችን ይመድባል፡ ላቦራቶሪዎችን ያቋቁማል፡ ያደራጃል፡ ያስተዳድራል፡ የዕፅዋትን ዘር ጥራት ይመረምራል፡ ይቆጣጠራል፡

፰· ለሚመደበው ማንኛውም የዕፅዋት ዘር ኢንስፔክተር የኤጀንሲው ኢንስፔክተር መሆኑን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ይሰጣል፡

፱· ማንኛውም የዘር ንግድ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግኝቶ በዘር ንግድ ላይ የተሰማራ ሰው ለተባለው ዘር የምስክር ወረቀት እንዲኖረው ፍላጎት ካለውና ከመለከተ ኤጀንሲው ያወጣቸው መስፈርቶች መሟላታቸውን አረጋግጦ የዘር ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡

፲· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት የተሰጠውን የዕፅዋት ዘር የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማጭበርበር ተግባር በመፈጸም ወይም የምሥክር ወረቀቱ የሚሰጥባቸውን ዝርዝር ሁኔታዎች ያለበቂ ምክንያት ተፈጻሚ ሳያደርግ ሲቀር ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን ጥሶ ሲገኝ የሰጠውን የዘር ጥራት የምስክር ወረቀት ይሰርዛል፡

፲፩· ኤጀንሲው ለውጭ አገር የዘር አረጋጋጭ ድርጅቶች እውቅና ሊሰጥ ይችላል፡

፲፪· ኤጀንሲው ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ሥልጣኑን በውክልና ለመስጠትና ውክልናው ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች ለመወሰን ይችላል፡

፲፫· ኤጀንሲው ለምርምርና ለምርት ተግባራት ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡና ወደ ውጭ ለሚላኩ ዘሮች የማስወጫና የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል።

፴፩· **የኢንስፔክተር ተግባርና ኃላፊነት**

ኢንስፔክተሩ በኤጀንሲው የሚመደብ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬ ስር የተመለከቱት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

## PART FOUR
## The Role of the Agency

29. *Duties and Responsibilities of the Release Committee*

Without prejudice to the provisions of this Proclamation, new variety of any plant is evaluated and released by the National Variety Release Committee (NVRC), composed of members assigned from appropriate bodies.

30. *Duties and Responsibilities of the Agency*

Without prejudice to the powers and duties vested on it under its establishment Proclamation, the Agency:

1) shall decide the type of varieties to be improted or locally produced;
2) shall prepare and issue the annual variety register, follow up and make sure that the register is received by users;
3) shall issue, renew, suspend, and cancel competence assurance certificate in matters related to production, processing, import and export, wholesale and retail of seed;
4) may establish seed testing centers for conducting tests on prescribed seed and may delegate those established or to be established centers;
5) shall perform seed testing by itself in accordance with the provisions of this Proclamation and appoint seed analysts;
6) may take at any time sample for analysis from any place of seed production, processing and from seeds ready for sale;
7) shall by establishing a team for inspection assign inspectors; establish, organize and administer laboratories, and carry out seed quality testing and control activities to enforce this Proclamation;
8) shall issue a certificate of authority to each assigned seed inspector that ascertain he is an inspector of the agency;
9) shall issue a seed quality assurance certificate to any person who, possesses a competence assurance certificate, is engaged in seed business and who desires to have certificate for the said seed and applies for it after assuring that such seed fulfills the Agency's prescribed ceriteria;
10) shall revoke the certificate issued under Sub–Article (9) of this Article, if the certificate issued has been obtained by misrepresentation as to the essential conditions or if the holder of the certificate has failed to comply with conditions under which the certificate has been issued or has violated any of the directives issued in accordance with this Proclamation;
11) may recognize any seed certification agencies established in any foreign country;
12) may delegate its power and decide the conditions upon which the delegation to be exercised for the implementation of this Proclamation;
13) shall give import or export permits for seeds to be imported or exported for research and production purposes.

31. *Duties and Responsibilities of the Inspector*

The inspector shall be assigned by the Agency and shall have the duties and responsibilities specified under Article 24 of this Proclamation.

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፴፪· የመተባበር ግዴታ**

በዚህ አዋጅ መሠረት ኢንስፔክተሩ ተግባሩን ማከናወን እንዲችል የሚመለከተው ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት።

**፴፫· ስለ አቤቱታ አቀራረብ**

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወሰዱ እርምጃዎች ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው፡ ውሳኔው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ይግባኙን አግባብ ላለው መደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

፪· አግባብ ባለው መደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ማንኛውም ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ እና አስገዳጅም ነው።

**፴፬· ስለቅጣት**

፩· ማንኛውም ሰው፡

ሀ) ሆን ብሎ ደረጃውን ያልጠበቀ የዕፅዋት ዘር ወይም ያልተመዘገበ የዕፅዋት ዘር ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ እንደሆነ ከ፲ ዓመት ባላነሰና ከ፲፭ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፶ ሺ በማያንስና ከብር ፻ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

ለ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፯ ከተደነገገው ውጭ የኢትዮጵያን ደረጃዎች ያላሟላ የዕፅዋት ዘር ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ እንደሆነ ከ፰ ዓመት ባላነሰና ከ፲ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፶ ሺ ባላነሰና ከብር ፻ሺ ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል።

ሐ) በዘር ማባዛት፡ ማዘጋጀት፡ ወደ ውጭ መላክ፡ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፡ ማከፋፈል፡ መቸርቸርና በጥራት ቁጥጥር ሂደት ላይ የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈጸም መደለያ ወይም ሌላ ስጦታ የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ እንደሆነ ከ፰ ዓመት በማያንስና ከ፲ ዓመት በማይበልጥ እሥራት እና ከብር ፶ ሺ በማያንስና ከብር ፻ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

መ) የከረጢት ስራቱ ደረጃውን ያልጠበቀ መሆኑን እያወቀ በተጠቀሰው ከረጢት የዕፅዋት ዘርን ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ እንደሆነ ከ፫ ዓመት ባላነሰና ከ፭ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፲፭ሺ በማያንስና ከብር ፳፭ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

ሠ) የተወሰደ ናሙና ወይም ለምርመራ የተሰጠ ናሙና በትክክል ምርቱን እንዳይወክል ሆን ብሎ ያዛባ እንደሆነ ከ፪ ዓመት ባላነሰና ከ ፭ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፳ሺ ባላነሰና ከብር ፴ሺ ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል።

ረ) በከረጢት ላይ የምልክት አደራረግና የከረጢቱ አስተሻሸግ ደረጃውን ያልጠበቀ ፡ በከረጢቱ ውስጥ ያለው የዕጽዋት የዘር ክብደት መጠን ከተከፈለበት ዋጋ ያነሰ የዕፅዋት ዘር ሆን ብሎ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ እንደሆነ ከ፪ ዓመት ባላነሰና ከ፭ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፲ ሺ ባላነሰና ከብር ፳ ሺ ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል ።

## PART FIVE
## *Miscellaneous Provisions*

32. *Duty to co-operate*

Any concerned person, if so required by the inspector, shall be bound to afford all necessary support in order to enable him to exercise his duties under this Proclamation.

33. *Appeal*

1) Any person aggrieved by measures taken pursuant to this Proclamation may appeal to an appropriate regular court within 30 days after he is notified of the decision.
2) Any decision made by a regular court shall be final.

34. *Penalties*

1) Any person who:
   (a) intentionally offers for sale or sells below standard or unregistered seed shall be punished with imprisonment of not less than 10 years and not more than 15 years and with a fine of not less than Birr 50 thousands and not more than Birr 100 thousands.
   (b) offers for sale or sells seed in violation of Article 17 of this Proclamation shall be punished with imprisonment of not less than 8 years and not more than 10 years and with a fine of not less than Birr 50 thousands and not more than 100 thousands.
   (c) gives or offers a gift or any other benefit to cause the commission of fraudulent act on seed production, processing, export, import, distribution, retail sell and quality control process shall be punished with rigorous imprisonment of not less than eight years and not more than ten years and with a fine of not less than Birr 50,000 and not more than 100 thousands.
   (d) knowingly offers for sale or sells seed in bags which do not comply with the standard shall be punished with imprisonment of not less than 3 years and not more than 5 years and with a fine of not less than Birr 15 thousands and not more than 25 thousands.
   (e) intentionally alters the sample drawn or delivered for test and thus resulting in an incorrect representation of the produce, shall be punished with imprisonment of not less than 2 years and not more than 5 years and with a fine of not less than Birr 20 thousands and not more than 30 thousands.
   (f) offers for sale or sells seeds in bags whose labeling and packaging do not comply with the standard and the weight of the seed in the bags is less than the amount paid for it, shall be punished with imprisonment of not less than 2 years and not more than 5 years and with a fine of not less than Birr 10 thousands and not more than 20 thousands.

፴፭· <u>ደንብን እና መመሪያዎች የማውጣት ሥልጣን</u>

፩· የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል ።

፪· ኤጀንሲው ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል ።

፴፮· <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች</u>

፩· የኢትዮጵያ የዕፀዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፮/፹፱ በዚህ አዋጅ ተሽሯል ።

፪· የኢንቨስትመንት እንዲሁም የንግድ ፈቃድና ምዝገባ አዋጆች በዕፀዋት ዘር ሥራ በተሠማራው ሰው ላይ እንደ አግባቡ ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

፫· ማንኛውም ሌላ ህግ ወይም የተለመደ አሠራር ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ።

፴፯· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

35. *Power to Issue Regulations and Directives*

1) The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.
2) The Agency may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation.

36. *Repealed Laws and Applicable Laws*

1) The Ethiopian Seed Council of Ministers Regulations, No. 16/1997 is hereby repealed.
2) The Investment and Commercial Licensing and Regisrations Proclamations shall be applicalbe to a person engaged in seed business, as the case may be.
3) Other laws or customary practices shall have effect with respect to matters covered by this Proclamation unless they are inconsistent with this Proclamation.

37. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of June, 2000.

Done at Addis Ababa, this 6th day of June, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA